# የሐይማኖት መከባበር እሴቶች፣ በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ ማሳያነት

***ሙሐመድ ሰኢድ ሙዙ**[1]*


አህጽሮተጽሁፍ

*የጥናቱ ዋና ዓላማ በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመከባበር መገለጫ እሴቶችን ማስተዋወቅ ነው። ጥናቱን ለማካሄድ ያነሳሳኝ ዋናው ምክንያት በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል በታሪክ የተገነባው የብዝሃ-ባህል የግንኙነት መስተጋብር ባሕርያት በዝርዝር ተጠንተው አልተገለፁም፤ ከነዚህ ተጠንተው ካልተገለጹ ባህላዊ እሴቶች መካከል አንዱ በቦረና ማህበረሰብ ያለው ሀይማኖታዊ የመከባበር እሴቶች ይገኙበታል። ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በገለጻ ስልት ተካሂዷል። መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ የዋሉት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታና ቃለመጠይቅ ናቸው። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት እሴቶቹ በሚገኙበት ባህላዊና ማህበራዊ ዓውድ ውስጥ ነው። አጥኚው ለስምንት ወራት ያህል መረጃዎችን ከአካባቢው ተመልክቷል። በታላሚ ንሞና ዘዴ የተመረጡ ስምንት ሰዎችም በቃለ መጠይቅ በመረጃ አቀባይነት ተሳትፈዋል። በጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋለው የጠቀሜታዊነት ፎክሎራዊ ንድፈ ሀሳብ ነው። በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ ለአብሮነት አስተዋጽዎ ያላቸው የመቻቻል እሴቶች በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ በሁለት ፎክሎር ዘውጎች (ሀገረሰባዊ ልማድ፣ማህበረ ፖለቲካዊ ተቋም) ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው። ይሄውም ሀገረሰባዊ መድሀኒት፣ ሀገረሰባዊ እምነትና ሀገረሰባዊ ጋብቻ በሀገረሰባዊ ልማድ ስር ይካተታሉ። እድር፣ ሀገረሰባዊ ዳኝነትና ጅጌ/አዝማች ደግሞ በማህበረ ፖለቲካዊ ተቋም ስር ይመደባሉ። በጥናቱ ውጤት መሰረት የሃይማኖት መከባበር እሴቶች ለቦረና ማህበረሰብ የአብሮነት፣ የእርስ በርስ ትስስር ማለት ነው። በቦረና ማህበረሰብ የጤና እክል የገጠመው ወይም አጋንንት የለከፈው ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ በልቡ አምኖ ጤንነቱን ለማግኘት ወደነዚህ የፀበል ቦታዎች ይሄዳል። ከጸበላቸው አልፎ እምነታቸውን ይቀበላል፤ በመስቀሎቻቸው ይታሻል።ከጋብቻ አንጻርም የክርስትና ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆን የጋብቻ መስፈርት አይሆንም። የ ሙስሊም ልጅ የክርስቲያን ልጅ፥ የክርስቲያን ልጅ የሙስሊም ልጅ ታገባለች፤ ያገባል። ሽማግሌዎች*

*በአዋቂነታቸው፣በታማኝነታቸው፣በትዕግስታቸውና በማህበራዊ ደረጃቸው መሰረት ይመረጣሉ። ሽማግሌዎቹን ለመምረጥ እስላም ወይም ክርስቲያን መሆን በመስፈርትነት አይወሰድም፤ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ለብቻው ቅሬ ወይም እድር የለውም፤ ሁለቱም ይሳተፋሉ። ክርስቲያኑ፤ ሙስሊሙ ልጁን ሲድር፣ ሙስሊሙም ክርስቲያኑ ሲድር አዝማች ይዞ ከባለጉዳዩ ጋር ለሙስሊም ወይም ለክርስቲያን እንግዶች ድግስ ያዘጋጃል። ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ያለምንም የሀይማኖት ልዩነት ማህበረሰቡ ተከባብሮና ተቻችሎ በአብሮነት እንዲኖር አስችሎት ቆይቷል፡*


**ቁልፍ ቃላት፤**ሀገረሰባዊ-ልማድ፣ ማህበረፖለቲካዊ ተቋማት፣ ጅጌ/አዝማች፣ እቅሬ

[1] MA. In Folklore and Literature, መቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ Email; muzuseid2011@gmail.com

# 1. መግቢያ

## 1.1 የጥናቱዳራ

በኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች ምናልባትም በዓለማችን ልዩ ባህርይ ያለው የመቻቻል እሴት ፈጥረው ለዘመናት መኖራቸውን ምሁራን ይገልጻሉ(አብዱላህ 2012፣Abbik 1998፣Braukamper 1992)።ኢትዮጵያ ባህለ-ብዙ ሀገር ነች።ባህለብዙነት ከሚገለፅባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ በአንድ ሀገር ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖቶች አብረው መኖራቸው ነው። የብዝሃ-ባህል ግንኙነት መስተጋብር ከሚገለፁባቸው እሴቶች መካከል ደግሞ አንዱ“መቻቻል” ነው። በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል በታሪክ የተገነባው የብዝሃ-ባህል የግንኙነት መስተጋብር ሁሉም ባሕርያት በዝርዝር ተጠንተው አልተገለፁም። ከነዚህ ተጠንተው ካልተገለጹ ባህላዊ እሴቶች መካከል ሀይማኖታዊ የመከባበር እሴቶች ይገኙበታል። የጥናቱ ዋነኛ አነሳሽ ምክንያትም የመከባበር እሴቶች *ተጠንተው* አለመገለጽ ነው። የዚህ ጥናት ትኩረት በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ የክርስትናና የእስልምናሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰብ መካከል ያለውን የመ ከባበር እሴት ከፎክሎር ዕይታ አንፃር ማጥናት ነው።

የመቻቻልና መከባበር ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ ከቤተ-መንግስት እስከ ቤተ-እምነት፤ ከልሂቃኑ እስከ ብዙሃኑ የጋራ ርዕሰ ጉዳይ በመሆን በተደጋጋሚ ሲነገር ይሰማል። ነገር ግን እነዚህ አካላት የመቻቻልና መከባበር ጽንሰ ሀሳብን የሚገልጹት ጽንሰ ሀሳቡን እንደተረዱበት መንገድ፣ እንደ እይታቸውና እምነታቸው ወይም እንደየግል ፍላጎታቸውና እንደሚያራምዱት አጀንዳ መጠን ነው (ጌታዋ፣ 2008፡1)።

መከባበር የግለሰብ መብትን እና ሰብአዊነትን በማወቅ ላይ የተመሰረተ ነው ይህም ማለት እርስ በርስ በሚኖረን ግንኙነት አንዳችን ለሌላው አሳቢነት እናሳያለን። ባላቸው ውስጣዊ እሴት እና ክብር ምክንያት ግለሰቦች መከበር አለባቸው (Lian and et.al. 2012)።

መቻቻል በኢትዮጵያ ምንም እንኳ የብዙሃን አጀንዳና በየዕለቱ ተደጋግሞ ሲነገር የሚደመጥ ርዕሰ ጉዳይ ቢሆንም ብዙሀኑን የሚያግባባና የሚያስማማ ጽንሰሀሳብ አይደለም። እንደ ጌታዋ (2008:53) ገለጻ መቻቻል የሚለው ጽንሰሀሳብ አንድምታው በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ነው። ለምሳሌ መቻቻል በጥሬ ትርጉሙ “ጥሩ ነገር አይደለም ግን ቻለው! ዋጠው! ወይም ታግሰህ አሳልፈው! አለያም ሆድ ከአገር ይሰፋል እንደሚባለው

ነገሩን ለፈጣሪ ሰጥተህ ተወው! ወዘተ” እንደማለት ነው:: በዚህ አሉታዊ ፍቺ መሰረት መቻቻል የሚለው ጽንሰሀሳብ ታጋሹ ትዕግስቱ እያለቀ ሲሄድ “በቃ! እስካሁን ድረስ ታግሻለሁ! ትዕግስትም ልክ አለው! እስከመቼ ድረስ እታገሰዋለሁ! እችለዋለሁ! እለማመጠዋለሁ! ወዘተ” ብሎ ወደ ግጭት ሊያመራ እንደሚችል ወይም የግጭት መንስኤ ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁም አንድምታ አለው።

የመቻቻል ጽንሰሀሳብ አወንታዊ አንድምታም አለው። “መቻቻል” የሚለውን የአማርኛ ቃል ደስታ ተክለወልድ፤ አዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት (1962፡1278) መሸካከም፣ መወሳሰን፣ መጣመር” ሲል ይፈታዋል። በዚህ መሰረት መቻቻል ማለት መረዳዳት፣ መደጋገፍ፣ መተጋገዝ፣ መተሳሰብ፣ መተዛዘን፣ ከእኔ ይልቅ ላንተ (አንተ-ትብስ፣ አንቺ ትብሺ) መባባል የሚሉትን ጽንሰሀሳቦች ያዘለ ትርጉም አለው። ይህ ጥናት በተካሄደበት በረና ማህበረሰብ “መቻቻል” ሙሉ በሙሉ አወንታዊ መልዕክት አለው። ይሄውም ማህበረሰቡ መቻቻልን አብሮ (አንድ ሆኖ፣ ተዋህዶ) መኖር የሚል ብያኔ ይሰጠዋል።

የፎክሎር ምንነትና ምድቦችን በሚመለከት ወጥና ሁሉን የሚያስማማ ብያኔና አከፋፈል የለም (ፈቃደ 1991፣ ሠሎሞን 2007)። እንደ ፈቃደ(1991) ገለጻ ፎክሎር የሰዎች መንፈሳዊና ቁሳዊ ባህል ሲሆን እርስ በርሳቸው የማይፈታ ዝምድና ባላቸው አራት አብይ ምድቦች ይከፈላል። እነሱም ስነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ናቸው። ሠሎሞን (2007፡59-60) በበኩሉ ፎክሎር በውስጡ በርካታ ጉዳዮችን እንደሚያካትትና በአራት ምድብ ማጠቃለል እንደሚከብድ በማስረዳት በስድስት ምድቦች (ስነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ውክልናና ማህበረ ፖለቲካዊ ተቋም) ከፍሏቸዋል። ይህ ጥናትም የሠሎሞን (2007፡59-60) የፎክሎር ዘውግ አመዳደብን መሰረት አድርጎ ተካሂዷል። ሃይማኖታዊ መቻቻል በአንድ አካባቢ በጉርብትና በሚኖሩ በተለያየ የሃይማኖቶች ተከታይ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የመቻቻል አንዱ ገጽታ ሲሆን የፎክሎር አንዱ አብይ ዘርፍ በሆነው በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ይጠናል።

ማንም ሰው የሱ የሆነ ነገር ሁሉ እንዲከበርለት ይፈልጋል። ስለዚህ የሌላውንም ማክበር ይጠበቅበታል። ይህ ሲሆን መከባበር ይፈጠራል። መከባበር ሐሳብን፣ አኗኗርን፣ ስራን፣ ምርጫን፣ውሳኔን ወዘተ. ያካትታል። መከባበር የቃልና የሽንገላ ሳይሆን በተግባር ሊገለፅ ይገባዋል። መከባበር ለማንኛውም ነገር ዋጋ መስጠት ስለሆነ የትልቅነት ምልክት ነው (የኢትዮጵያ ኃይማኖቶች ጉባኤ፣2014) ።

የተለያዩ ሃይማኖቶች ያሏቸው የአንድ ሀገር ህዝቦች በልዩነቶች ምክንያት ወደ ግጭት እንዳይገቡ ለመ ከላከል ከሚረዱ መፍትሄዎች አንዱ መቻቻልና የመቻቻል እሴቶችን በጥልቀት ማጥናት እና ማስተዋወቅ ነው። ይህን እውን ለማድረግም የሃይማኖት መቻቻልና መከባበር ፅንሰ-ሀሳብ በየእለቱ በሚደረጉ ባህላዊ ክዋኔዎች አማካይነት ልዩነትን አክብሮ አብሮነት እንዴት ጎልቶ እንደሚወጣ በጥናት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህ ጥናትም ተጠኚው ማህበረሰብ የፈጠራቸው፣ያዳበራቸው ሆኖም እየደበዘዙ ያሉ የሃይማኖት መቻቻልና መከባበር መገለጫ የሆኑ ባህላዊ እሴቶችን በመለየት ለማስተዋወቅ አስተዋጽኦ አለው። መቻቻልና መከባበር ሰፊ ጽንሰሀሳብ በመሆኑም ጥናቱ በሃይማኖት ልዩነት ያላቸው ማህበረሰቦች በአብሮነት መኖራቸውን የሚያሳዩ እሴቶች ላይ ብቻ ያተኩራል።

1.2 የጥናቱዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመከባበር መገለጫ *እሴቶችን* በመለየት ማስተዋወቅ ነው።

## 2. የጽንሰሀሳብ መነሻና የጥናቱ ዘዴ

### 2.1 የመቻቻል ጽንሰሀሳብ

የመቻቻልና መከባበር ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ ከቤተ-መንግስት እስከ ቤተ-እምነት፤ ከልሂቃኑ እስከ ብዙሃኑ የጋራ ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ በተደጋጋሚ ሲነገር ይሰማል። ሆኖም እነዚህ አካላት መቻቻልና መከባበርን የሚገልጹት ጽንሰ ሀሳቡን እንደተረዱበት መንገድ፣ እንደእይታቸውና እምነታቸው ወይም እንደግል ፍላጎታቸውና እንደሚያራምዱት አጀንዳ መጠን ነው (ጌታዋ፣ 2008፡1) ።

ምንም እንኳ መቻቻል በኢትዮጵያ የብዙሃን አጀንዳና በየዕለቱ ተደጋግሞ ሲነገር የሚደመጥ ርዕሰጉዳይ ቢሆንም ብዙሀኑን የሚያግባባና የሚያስማማ ጽንሰሀሳብ አይደለም። መቻቻል የሚለው ጽንሰሀሳብ አንድምታው በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ነው። መቻቻል የሚለው ጽንሰሃሳብ አሉታዊ አንድምታ ያለውን ያህል አወንታዊ ፍች አለው። እንደዩኒስኮ የመቻቻል ብያኔ “መቻቻል የሞራል ግዴታ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊና ህጋዊ ቅድመ ሁኔታ ጭምር ነው። ለሠላም መስፈን አስፈላጊ ምግባር የሆነው መቻቻል ግጭትን በሰላም እሴት ለመቀየር የራሱን አስተዋጽዎ ያደርጋል። እንደዩኒስኮ ገለጻ መቻቻል፤ሽንፈት፣ውርደት ወይም ጥቅምን አሳልፎ መስጠት አይደለም። መቻቻል ዓለምአቀፍ ሰብዓዊ መብቶችንና የሌሎችን መሠረታዊ ነጻነቶች እውቅና ከመስጠት የሚመነጭ አዎንታዊ አመለካከት ነው (UNESCO፣ 1995፡87)።

እንደMurphy (1997) ገለጻ ደግሞ ፣መቻቻልና መከባበር በአንድ ሰው ፈቃደኝነት የተለያዩና ተቃራኒ የሆኑ ሀሳቦችን የመቀበል፣ የአንድ ግለሰብ /ቡድን እምነት (አመለካከት) እውነተኛ መሆን አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ፍርድ ከመስጠት መቆጠብ ነው። መቻቻልና መከባበር የአንዱ ወገን እምነት እውነትነት የሌለው ውሸት ወይም በተቃራኒው ነው ብሎ ገለጻ ከመስጠት የተቆጠበ ነው።

የመከባበር ፅንሰሀሳብ ከመልካም አተያይ ጋር የተቆራኘ የማህበራዊ ግንኙነት መስተጋብር ነው። መከባበር ከግለሰብ እስከ ቡድን እንዲሁም ከሀገር እስከ መንግስታት የሚገለፅ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው። በመሆኑም መቻቻልን በፅንሰሀሳብ ደረጃ እንዲህ ነው ብሎ ከመተንተን ይልቅ በቡድኖች መካከል ባለ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ግንኙነት ላይ ተመስርቶ ማጥናት የተሻለ ነው።

መቻቻልና መከባበር ከሚታይባቸው ጉዳዮች መካከል የተለያ የሃይማኖት ተከታይ ቡድኖች ይገኙበታል። ይህም የሃይማኖት መቻቻል ጽንሰሀሳብ በሚል ይታወቃል በሃይማኖት መቻቻል ጽንሰሀሳብ መሰረት “የሌሎችን ሃይማኖት ከራሳችን ሃይማኖትጋር በማንኛውም መለኪያ ብናነፃጽረው ‘መጥፎ ነው!’ የምንልበት መለኪያ የለንም” (Newman፣ 1978)። ሃይማኖታዊ መቻቻል በአንድ አካባቢ በጉርብትና በሚኖሩ በተለያየ የሃይማኖቶች ተከታይ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የመቻቻል አንዱ ገጽታ ሲሆን የፎክሎር አንዱ አብይ ዘርፍ በሆነው በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚጠናነው። አብሮነት ሁለት ቡድኖች ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድነት ሲኖሩ የሚፈጥሯቸው የጋራ ጉዳዮች

ሲገናኙ የሚኖረውን ግንኙነት ሰላማዊነት የሚያሳይ ነው። መቻቻል ደግሞ በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል ልዩነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ጉዳይ አብሮ መሆንን ያሳያል።ሰዎች አብሮ በመኖር ሂደት ተሞክሮ ያገኛሉ። በተሞክሯቸውም ምን መስራትና አለመስራት እንዳለባቸው ያውቃሉ። “አብሮነት”የተሻለ የኑሮ ግንኙነት ስልት ለመፍጠር ማህበራዊ መተሳሰብን ለማጠናከርና አካባቢን ምቹ ለማድረግ የሚያግዝ የመቻቻል ባሕርይ ነው። መቻቻልና መከባበር ሁለትና ከዚያ በላይ ቡድኖች መኖራቸውን የሚያመለክት ነው። በመሆኑም አብሮነት እነዚህ ቡድኖች በሰላም አብረው ለመኖር አንዱ የሌላውን እምነትና ድርጊት አክብሮ መገኘትን ያሳያል።

## 2..2. የጥናቱ ዘዴ

### 2..2..1. የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ ንድፍ ከአይነታዊ ምርምር የሚመደብ ሲሆን ገላጭ የምርምር ስልትን ተከትሎ ተካሂዷል።የጥናቱን ዓላማ ለማሳካትም የዲስኩር ትንተናን እንደጥናት ማካሄጃ ተጠቅሟል።

### 2..2..2. የመረጃ ምንጭና የንሞና ዘዴ

የመቻቻል ባህርያትን ለመረዳትና ባህላዊና ማህበራዊ የመከሰቻ ገጽታዎችን ለመተንተን በአውድ ላይ የተመሠረቱ አይነታዊ መረጃዎችን መጠቀም ይጠይቃል። በመሆኑም ጥናቱ ከተጠኘው ህዝብ እይታ አንፃር መረጃ ለማሰባሰብ “ቀዳማይ” የመረጃ ምንጭ(ምልከታና ቃለመጠይቅ) እንዲሁም ጽንሰሀሳቡን በሚመለከት ያሉ እይታዎችን ይበልጥ ለመረዳትና ለማጠናከር ዳህራይ የመረጃ ምንጭ (ከተለያዩ ጽሁፎችና በሌሎች ጸሀፍት የተዘጋጁ መጻህፍት) ተጠቅሟል። በመሆኑም ለቃለመጠይቅ በታላሚ ንሞና ዘዴ (ከሁለቱም እምነት ተከታይ) ስምንት ሰዎች ተመርጠዋል።

### 2..1.2. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በጥናቱ የመቻቻል እሴት መገለጫዎችን በሚመለከት መረጃዎች በምልከታና በቃለ-መጠይቅ ከተሰበሰቡ በኋላ መረጃ አቀባዮቹ የሰጧቸው መረጃዎች በየአይነታቸው ተደራጅተዋል። በመቀጠልም የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመከባበር መገለጫ ፎክሎሮችን ለማስተዋወቅና እየተከሰቱ ያሉ ለውጦችን ለመግለጽ የዲስኩር ትንተና ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። ምክንያቱም የዲስኩር ትንተና ዘዴ በአካባቢው ያለውን የመከባበር እሴት በአግባቡ ለማስረዳት ይበልጥ ስለሚያስችል ነው።

## 3.አካባቢያዊ ዳራ

ለጥናቱ የተመረጠው አማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ነው። በደቡብ ወሎ ዞን 22 ወረዳዎች ይገኛሉ። በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል አንዱ በረና ነው። የበረና ወረዳ ከደቡብ ወሎ ዞን ዋና መዲና ደሴ ከተማ 180 ኪ.ሜ. ርቀት በምዕራብ፣ ከክልሉ ርዕሰ መዲና ከባህር ዳር 285 ኪ.ሜ. ርቀት በምስራቅ እንዲሁም ከአዲስ አበባ 460 ኪ.ሜ. ርቀት በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ይገኛል። ወረዳውን ከሚያዋስኑ ጎረቤት ወረዳዎች

በምእራብ ምስራቅ ጎጃም ዞን፣ በምስራቅ ለጋንቦ ወረዳ፣ በሰሜን ምስራቅ ሳይንት ወረዳ፣ በደቡብ ወግዲ ወረዳ ያዋስነዋል፡፡

የቦረና ወረዳ ፕላን ኮሚሽን (2015) እስታስቲክስ መረጃ እንደሚያመለክተው የቦረና ወረዳ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 200,378 ሲሆን የቆዳ ስፋቱ ደግሞ 1,000 ኪ.ሜ. ስኩየር ነው፡፡ የቦረና ወረዳ በ 34 የገጠር ቀበሌዎችና 4 የገጠር ከተሞች የተዋቀረ ነው፡፡ የአየር ንብረት በተመለከተ ደጋ 20%፣ ወይና ደጋ 47%፣ ቆላ 32% እና ውርጭ 1% ሲሆን የሙቀት መጠን 26$^{O}$C-11 $^{O}$C ድግሪ ሴንቲ ግሬድ ነዉ፡፡ አማካኝ የዝናብ መጠን ከ500 – 1400 ሚሊ ሊትር ነዉ፡፡

የወረዳው ነዋሪዎች የክርስትና (ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ የመካነ እየሱስ፣ የካቶሊክ እና ጅሆባ ዊትነስ) እና የእስልምና ሃይማኖቶች ይገኛሉ፡፡ በወረዳው ውስጥ 16 የከተማ እና ከ 80 በላይ የገጠር እድሮች /ቅሬዎች/ ይገኛሉ፡፡ እያንዳንዳቸው እድሮች በአማካይ ከ 900 – 1500 አባላት አሉት (የቦረና ወረዳ ፕላን ኮሚሽን፣ 2015)፡፡

የወረዳው ነዋሪዎች የሃይማኖት ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ምክንያት ህብረት ይፈጥራሉ፡፡ ማህበራዊ ግንኙነቱን ለመፍጠርም ሆነ የተመሠረተው ግንኙነት ቀጣይነት እንዲኖረውና መሠረት እንዲይዝ የሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች ሚናቸው ከመከባበር እሴት አንጻር ተመጣጣኝ ነው፡፡ ማህበራዊ መስተጋብሮቹ በኑሮ ውስጥ አንዱ ወደ ሌላው በተለያዩ ምክንያቶች በመሄድ ይገናኛሉ፡፡

## 4. የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች

በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ ለአብሮነት አስተዋጽዎ ያላቸው የመከባበር እሴቶች በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ በሁለት ምድብ (ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ማህበረፖለቲካዊ ተቋም) ስር ይከፈላሉ፡፡ የማህበረሰቡ ዋና ዋና የመቻቻል እሴቶች ሀገረሰባዊ መድሀኒት፣ ሀገረሰባዊ እምነት፣ ሀገረሰባዊ ጋብቻ፣ እድር፣ ሀገረሰባዊ ዳኝነትና ጅጌ/አዝማች ናቸው፡፡ እነዚህን እሴቶች ከምድቦቻቸው አንጻር ስንመለከታቸውም ሀገረሰባዊ መድሀኒት፣ ሀገረሰባዊ እምነትና ሀገረሰባዊ ጋብቻ በሀገረሰብ ልማድ ስር ይካተታሉ፡፡ ቀሪዎቹ እድር፣ ሀገረሰባዊ ዳኝነትና ጅጌ/አዝማች ደግሞ በማህበረፖለቲካዊ ተቋም ስር የሚመደቡ ናቸው፡፡

ማህበረሰቡ እነዚህን ባህላዊ የመከባበር እሴቶች መገለጫ ካለፈው ትውልድ ተቀብሎ ዛሬም ይከውናቸዋ ል፤ይኖራቸዋል።

## 4.1. ሀገረሰባዊ ልማድ

### ሀ. ሀገረሰባዊ መድሀኒት

ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው መንፈሳዊ የህክምና ግብዓቶችን በመጠቀም የጤና ችግሮችን ለመፍታት የሚከወኑ ድርጊቶች የሀገረሰብ ህክምና ስር ይመደባሉ።በዚህም የተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ በሚገኙ እምነቶችና ሀ ይማኖቶች የአስተምህሮ ስርዓት መሰረት እንደመስቀል፣የሀይማኖት መጽሐፍ፣ጸበል፡ዘምዘም፡ክታብ ወዘተ በመጠቀም በቅዱስ ስፍራዎች እንደቤተክርስቲያን መስጊድ፣የጸበል ቦታ፡ሀገረሰባዊ ሀይማኖቶች የሚከወኑ በት ስፍራ ወዘተ ትልቅ ስፍራ በሚሰጣቸው ግለሰቦች በሚደረጉ ጸሎቶች፣ለፈጣሪያቸው ወይም ሌላ ህመም ን ያመጣል ብለውለሚያምኑበት አካል በሚያቀርቧቸው መስዋዕቶችና መሰል መንፈሳዊ ድርጊቶች አማካኝነ ትየተለያዩ በሽታዎችን የመለየትና የመፈወስ ስርዓቶች ያካሂዳሉ(ሠሎሞን፣2007)። በቦረና ወረዳም በሀገረሰባዊ መድሃኒትነት ከሚያገለግሉ እሴቶች መካከል አንዱ የጸበል ስፍራዎች ናቸው።

በቦረና ወረዳ በርካታ የጸበል ስፍራዎች ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል ሚካኤል፣ትክል ድንጋይ፣ ቅድስት አርሴማ፣ ምስካቤ ቅዱሳን፣ አማኑኤል፣ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ፣ ልደታ ማሪያም፣ ኪዳነምህረት፣ ዳቦ ገዳም መድሃኒዓለም፣ ገብረክርስቶስ ወዘተ ይጠቀሳሉ።

በቦረና ማህበረሰብ የጤና እክል የገጠመው ወይም እርኩስ መንፈስ የተጠናወተው፣ አጋንንት የለከፈው ወዘተ ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ በልቡ አምኖ ጤንነቱን ለማግኘት ወደነዚህ የፀበል ቦታዎች ይሄዳል። ከጸበላቸው አልፎ እምነታቸውን ይቀበላል፤ በመስቀሎቻቸው ይታሻል። እንደ ቀሲስ ፍቅረማሪያም ገለጻ፣ ጸበል መጠመቅ በክርስትናው በኩል የሚገኝ እምነታዊ-ሀይማኖታዊ ህክምና ሲሆን አገልግሎቱ ለሙስሊሙ ጭምር ነው። ይሄውም ክርስቲያኑ ለሃይማኖታዊ ስርዓቱና ለጤንነቱ ሲል ጭምር የሚፈጽመው ሲሆን ሙስሊሙ ለጤንነቱ ፈውስ ማግኛ ሲል የሚገለገልበት ነው።

ሙስሊሞቹ ይህንን የሚያደርጉት ቅድመ አያቶቻቸው፣ አያቶቻቸውና አባቶቻቸው በዚህ ፎክሎራዊ እሴት ተጠቅመው መፈወሳቸውን ስለሚያውቁ ነው። ስለዚህ ምንም እንኳ ኋላ ላይ ተምረውና አምነው ሀይማኖቱን ለመቀበል የሚጠመቁ ቢኖሩም እንኳ ጸበል መጠመቅ ለብዙሃኑ ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ ጉዳይ

ሳይሆን ባህል፣ ወግና ልማድ ነው። በዚህ መሰረት ጸበል መጠመቅ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ እሴት ነው። በመሆኑም በቦረና የጸበል ቁምነገሩ ጸበሉን የሚጸበለው አካል ክርስቲያን ወይም ሙስሊም መሆኑ ሳይሆን፣ በጸበሉ ተጠምቆ ለመፈወስ ያለው ልባዊ ፍላጎት ነው(ቀሲስ ፍቅረማሪያም፣ ቃለመጠይቅ መጋቢት16/2016 ዓ.ም)።

በመሆኑም በቦረና የሚገኙ ሙስሊሞች በሁሉም የጸበል ቦታዎች (ከገብረክርስቶስ ጸበል በስተቀር) ገብተው ይጠመቃሉ፤ አጥማቂ ካህናትም የጥምቀት አገልግሎቱን ያለምንም ልዩነት ይሰጣሉ። ሆኖም ገብረክርስቶስ ጸበል ገብቶ ለመጠመቅ የክርስትና እምነት ተከታይ ሆኖ መገኘት የግድ ይጠበቅባቸዋል። ይህም የጸበል ቦታው 2013 ዓ.ም የተጀመረ ከመሆኑ አንጻር ቀደም ባሉ ዓመታት በጸበል ተጠምቆ የመዳን እሴቱ ለክርስቲያንና ለሙስሊም ያለምንም ልዩነት ይፈጸም እንደነበር ያሳያል። ሆኖም አሁንም ድረስ ሙስሊም ክርስቲያኑ ከገብረክርስቶስ ጸበል በስተቀር ሌሎች ጸበል ቦታዎች ላይ በመሄድ ይጸበላሉ፤ ይፈወሳሉ።

### ለ. ሀገረሰባዊ እምነት

ማህበረሰቡ መልካም ህይወት ለመኖር ይጠቅመኛል ብሎ በዕለት ዕለት ሕይወቱ የሚከውናቸው፣ እንዲህ ቢሆን ችግር ይገጥመኛል ብሎ የሚፈራቸው፣ ይህን ባደርግ ደግሞ የተሻለ ነገር ይገጥመኛል በሚል የውስጥ መንፈሳዊ እምነት የሚከውናቸው በርካታ ልማዶች አሉ። የእነዚህ ሀገረሰባዊ እምነቶች መነሻቸው ሃይማኖታዊ ሳይሆን የማህበረሰቡ ባህል ነው።

በሀገረሰባዊ እምነት ዘርፍ ስር የሚመደቡት በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ተፈጥሯዊ ሁነቶች ለምሳሌ ዝናብ፣ፀሐይ፣በረዶ፣መብረቅ ወዘተ ሀይል አላቸው(በተፈለገው መንገድ ማዘዝ ይችላሉ)፤ ተብለው በሚታመኑ ግለሰቦች አማካኝነት የሚከወኑ እምነቶች ናቸው። በአገራችን ተፈጥሮን ለመቆጣጠር በሚል የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች በርካታ ናቸው። ከእነዚህም መካከል በክረምት ወቅት በረዶ እንዳይጥልና ሰብል እንዳያበላሽ በሚል የሚሰራ ተፈጥሮን የመቆጣጠሪያ አ ስማት (ጸሎተበረድ)፣በረዶ በሚፈለገው (በተወሰነ)ቦታ ላይ ብቻ እንዲጥልበሚል የሚደረግ ጸሎት አለ (ሠሎሞን፣ 2007)።

በቦረና የሚገኙ ማህበረሰቦችም በአካባቢያቸው የሚከሰቱ በረዶና የዝናብ መብዛት ችግሮችን ለመቅረፍ ሀገረሰባዊ እምነቶችን ይተገብራሉ። ለምሳሌ በወረዳው ቆላማ አካባቢ የሚገኙ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በአንድ ላይ የበረዶ (የበላ) ጠባቂ በሚል ገንዘብ አዋጥተው በአካባቢው ወደሚገኝ የተከበረ የሃይማኖት ቦታ

(የታወቀ ቦታ) በመሄድ ያዋጡትን ገንዘብ ሰጥተው በጋራ ጸሎት አስደርገውና አድርገው ይለያያሉ። በደጋው አካባቢው ደግሞ በአካባቢው ወደታወቁ የበረድ ደጋሚዎች፣ ጠባቂዎችና ቂጣ ሰቃዮች በመሄድ ያዋጡትን ገንዘብ በመስጠት እምነት ስርዓቱን ያስፈጽማሉ። በመጨረሻም ምርቱ ተሰብስቦ ሲያልቅ የበረድ ጠባቂ ተብሎ ከሙስሊሙም ከክርስቲያኑም ማህበረሰብ እህል ተሰብስቦ ይሰጣል። በዚህ ሂደት እርስ በእርስ መከባበር እንጂ አንድም ተቃውሞ አይደመጥም (አቶ አህመድ ሙህዬ እና አቶ የሱፍ ገዛኸኝ፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016 ዓ.ም)። ይህም የቦረና ማህበረሰብን ሙስሊምና ክርስቲያን አንድ ሆኖ በመከባበርና በመቻቻል አብሮ እንዲዘልቅ አስተዋጾ አለው።

**ሐ. ሀገረሰባዊ ጋብቻ**

ጋብቻ በክርስቲያኑም በሙስሊሙም ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ አለው። በቦረና ማህበረሰብ የክርስትና ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆን የጋብቻ መስፈርት የማይሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው።በቦረና የሙስሊም ልጅ የክርስቲያን ልጅ፡የክርስቲያን ልጅ የሙስሊምልጅታግባለች፤ያገባል።በዚህ ሂደ ት በጋብቻወቅት ወይም ኋላ ሙስሊሙ ወደ ክርስትና ወይም ክርስቲያኑ ወደ እስልምና ሃይማኖት ይቀይራል። አልያም ሁለቱም የየግል ሃይማኖታቸውን እንደያዙ በጋብቻ ተጣምረው አብረውይኖራሉ።

ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ፤ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጋር ይጋባል። ማህበረሰቡ ምናልባት ዘር ይቆጥር ይሆናል። ዘር የሚቆጠሩበት ምክንያት አንዱ ለአጥንት ጉዳይ ሲሆን ሌላው ደግሞ በስጋ ዝምድና የማይገናኙ መሆኑ ን ለማረጋገጥ ነው። ከአጥንት ጉዳይ ጋር ተያይዞ የቡዳ ወይ የባሪያ ዘር አለመኖሩን ያረጋግጣሉ::ከዚህ ው ጪ በአጥንቱም በሃብቱም ይመጥናል ለሚለው እስላሙ ለክርስቲያኑ፣ክርስቲያኑ ለእስላሙ ልጁን ይድራል፤ ይዋለዳል። በሠላምና በፍቅር በጋራ ይኖራል። በቦረና በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ግማሹ ሙስሊም ግማሽ ክር ስቲያን ሆኖ ይኖራል፤ባል ወይም ሚስት አንዱ የቄስ ሌላው የሼህ ልጅ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲህ በፍቅር በመኖር የወለዷቸውም ልጆች የመረጡት ሀይማኖት ተከታይ ሆነው ያድጋሉ፤ እንደምርጫቸው ሙስሊም ወይም ክርስቲያን ሊያገቡና ሊወልዱም ይፈቀድላቸዋል (አቶአህመድ ሙህዬ እና አቶ የሱፍ ገዛኸኝ፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016 ዓ.ም)።

በቦረና እስላም ከክርስቲያኑ ጋር ተጋብቶ ተዋልዶ ይኖራል። ክርስቲያን ሆኖ፡እስላም ዘመዶች አሉት። እስላ ም ሆኖ፣ቄስ ዘመዶች አሉት። በቦረና የጋብቻ ባህል የሃይማኖት አባቶችና የእምነቶቹ ተከታዮች የልዩነት ሳይ

ሆን፤የአንድነት ተግባራዊ መገለጫ ሆነው ቆይተዋል። በመሆኑም የጋብቻ መስፈርት በቦረና የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ ተምሳሌት ነው (ቀሲስ ፍቅረማሪያም ቃለመጠይቅ መጋቢት16/2016 ዓ.ም፣ አቶ የሱፍ ገዛኸኝ፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016 ዓ.ም)።

## 4.2 ማህበረ ፖለቲካዊ ተቋማት

### ሀ. ሀገረሰባዊ ዳኝነት

በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ወንጀሎችና ግጭቶች ተባብሰው የከፋ አደጋ ከማድረሳቸው በፊት በአካባቢ ው በሚታወቁና በጋራ ስምምነት በተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎች መፍትሄ እንዲያገኙ ይደረጋሉ። ሽምግል ና በሀገረሰባዊ የዳኝነት ተቋም ስር ይመደባል። ሀገረሰባዊ የዳኝነት ተቋማት ለማህበረሰቡ ዘላቂ ሰላም በመፍ ጠር ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው (ሠሎሞን፣ 2007)።

በቦረና ማህበረሰብ ውስጥም ሽምግልና በአካባቢው የሚከሰቱ የስርቆት፣የንብረት ማጥፋት፣ የጸብ፣የግድያና መሰል ወንጀሎችን የፈጸሙ ግለሰቦችበህሉ በሚፈቅደው መሰረት ወንጀል ፈጻሚዎችን የማ ውጣጣት፣የመቅጣትና የማስታረቅ ስራዎችን በመስራት የተከሰቱ ችግሮችን በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ በመስጠት ሠላም እንዲሰፍን ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

በቦረና የሽምግልና ስርዓት ሽማግሌዎችበአዋቂነታቸው፣በታማኝነታቸው፣በትዕግስታቸው፣በማህበራዊ ደረ ጃቸውና በኢኮኖሚ አቅማቸው መሰረት ይመረጣሉ። ሽማግሌዎቹን ለመምረጥ እስላም ወይም ክርስቲያን መሆን በመስፈርትነት አይወሰድም፤ እስላምም ክርስቲያንም ሊመረጥ ይችላል። ሽማግሌዎች ወንጀሉን፣በደሉን ማን እንደፈጸመው ለማወቅ መሃላ በማስፈጸም፣በመራገም ወዘተ የተደበቀ ወንጀለኛንና በዳይን ይለያሉ።ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘውን ወገን ይቀጣሉ፤ተጎጂውንም ወገን ያ ስክሳሉ። ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ያለምንም የሀይማኖት ልዩነት ማህበረሰቡ ተቻችሎ በአብሮነት እንዲኖር አስችሎት ቆይቷል።

በቦረና ማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶች ዳኝነት የሚያገኙበት ሌላው ሀገረሰባዊ የዳኝነትተቋም "አቡወለድ" በመባል ይታወቃል። "አቡወለድ" አንድ የዘር ግንድ ያላቸው ሰዎች የሚመሰርቱት ተቋም ነው። እንደ አቶ አህመድ ገለጻ፣ "የአንድ ሰው ዘር ግንድ በአራት አቅጣጫ (በአባቱ አባት፣ በእናቱ አባት በአባቱ እናት እና በእናቱ እናት) ይወሰናል። በመሆኑም ሰውየው በነዚህ አራት አቅጣጫዎች ዘሩን በማጥናት "አቡወለድ"

ማህበር ይመሰርታል። ይህ “አቡወለድ” ማህበር ከየቦታው ተጠራርቶ በየአመቱ (በየመንፈቁ) እየተገናኘ ይገባበዛል፣ ይወያያል፤ የተቸገሩ ወገኖቹን ይረዳል፤ ያጋጠሙ ችግሮችን ይፈታል። አቡወለድ ማህበራት የሚመሰረቱበት ዓላማ በዘመዳሞች መካከል ጋብቻ እንዳይፈጠር መጠበቅ ነው። ሆኖም አብሮ በመኖር ሂደት የአቡወለድ አባል ጋር ግጭት ሊፈጠርና ፀብ ሊመጣ ይችላል። በቦረና በአቡወለድ አባላት መካከል የተፈጠረን ግጭት፣ ጸብ፣ ቅያሜ ለመፍታት የሀገር ሽማግሌ መምረጥ አያስፈልግም። ይልቁንም ተበዳይ ለአቡወለድ አባላቱ መንገር ብቻ ይበቃዋል። በዚህ ጊዜ አቡወለዱ ጉዳዩን አጣርቶ ችግሩን ከስር መሰረቱ እንዲፈታ (እንዲደርቅ) ያደርጋል” (ቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016 ዓ.ም)።

በቦረና ማህበረሰብ የአቡወለድ አባል ለመሆን እስላም ወይም ክርስቲያን መሆን መስፈርት አይደለም። የአቡወለድ በአካባቢው ሙስሊምና ክርስቲያን አማኞች በዘር ሀረጋቸው ብቻ በመቻቻልና በአብሮነት ለመኖር ያስችላቸዋል፤ ያስተሳስራቸዋል።

## ለ. ቅሬ/እድር

“ቅሬ” እድር እየተባለ ከሚጠራው ማህበራዊ ተቋም ጋር ተመሳሳይ ዓላማ ያለው ሲሆን የሚተዋወቁ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሠርቱት ባህላዊ ማህበራዊ ተቋም ነው። ቅሬ እንደ እድር ሁሉ ከሃዘንና መከራ ጋር ይገና ኛል። ቅሬ ከእድር የሚለየው ቅሬው ከቀብር መልስ እንጀራና ወጥ የሚያመጣው ከየቤቱ መሆኑ ነው። ከለቅ ሶ ባሻገር ቅሬም ሆነ እድር ሌሎች የተለያዩ ማህበራዊ ፋይዳዎች፣ደንብና ስርዓቶች አሏቸው።ለምሳሌ አቅም በፈቀደ መጠን በሃዘን ጊዜ ከቅሬ እንደማይቀር ሁሉ፣በደስታ (በሠርግ)ወቅት ቅሬ አይለይም፤በሁለቱ አካላት መካከል ፀብ(ቂም) ቢኖር እንኳን እርቅ ወርዶ የሃዘንም ሆነ የደስታ ተካፋይ እንዲሆኑ ይደረጋል። በተለይ በሃ ዘን ወቅት ያኮረፈው ከነኩርፊያው በጸበኛው ሰው ሃዘን ላይ ይገኛል።

አንድ እድር ሲመሰረት መስራቾቹ ከመተዋወቅ አልፎ የጋራ ፍላጎት ያላቸው ናቸው። ፍላጎቱ የሚመጣው በመቀራረብና አንዱ ሌላውን በማክበር በመተሳሰብ አንዱ ለሌላው መኖር እውቅናበመስጠት የሚጠነክር ነው። ዕድሮች በአባላት የመኖሪያ ሠፈርና በጾታ ላይ መሠረት አድርገው ይደራጃሉ ወይም ይቋቋማሉ። የወንድ፣የሴት፣የሰፈር፣የከተማ የሚሉ የዕድር ዓይነቶች አሉ። ሞት ድንገት ሲመጣ የሰው ልጅ አጋዥ ያስፈልገዋል።በማህበረሰቡ ባህል አንድ ሰው ሲሞት በብዙ ሰው አጀ ብ አስከሬን ወደ መቃብር በክብር ይሸኛል። የእንግዳ መሸኛ ድንኳን ይሠራል።

የሟችን የቅርብ ዘመዶች ያስተዛዝናል፤ ገንዘብ በማዋጣት ወጭውን ይጋራል። ይህን ማህበራዊ ኃላፊነት

መወጣት ደግሞ የእድሮች ዋነኛ ተግባር ነው። እድር/ቅሬ በቦረና ማህበረሰብ የክርስቲያኑና የሙስሊሙ የጋራ ማህበራዊ ተቋም ነው። በዚህ መሰረት በቦረና ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ለብቻው ቅሬ ወይም እድር የለውም።ክርስቲያኑም ሙስሊሙም በአንድ ቅሬ ውስጥ ይሳተፋሉ፤ አሁንም ድረስ እየተሳተፉም ይገኛሉ (አቶ አህመድ ሙህዬና አቶ የሱፍ ገዛኸኝ ቃለመጠይቅ የካቲት 12፣ ቀሲስ ፍቅረማሪያም መጋቢት16/2016 ዓ.ም)።

በቦረና የመጀመሪያዎቹ እድሮች መቼ እንደተመሰረቱ ባይታወቅም እስካሁን የነበረው ቀጥሎ አዳዲስ እየተ መሰረቱ በርካታ እድሮች ለተመሳሳይ ዓላማ በተለያየ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ዘልቀዋል። በድሮ ጊዜ ዕድሮቹ በቃል በሚተላለፉ ተግባራትና ደንቦች ነበሯቸው። በአሁኑጊዜ ደግሞ እያንዳንዱ ዕድር በፅሁፍ የሰፈረ መተዳደሪያ ደንብ አላቸው። እድር/ቅሬ በቦረና ማህበረ ሰብ የክርስቲያኑና የሙስሊሙ የጋራ ማህበራዊ ተቋም ነው። ማህበረሰቡ በአንድ ቅሬ ውስጥ ሲሰባሰብ የቅሬው ዳኛሙስሊሙ ወይም ክርስቲያኑ ሊሆን ይችላል።በቅሬው የአሰራር መርህ መሰረት ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ በወቅቱ ያለው የእድር ዳኛ ይቀጣዋል። ማህበረሰቡም ያለምንም የሀይማኖት ልዩነት ቅጣቱን አሜን ብሎ ይቀበላል እንጂ የእድር ዳኛውን ማንነት በማንሳት ቅሬታ ውስጥ አይገባም።ቅጣት የተፈረደበት የእድር/ቅሬ አባልም “ለምን ተቀጣሁ?”፣ “ዳኛው ሙስሊም ስለሆነ ነው” ወይም “ዳኛው ክርስቲያን ስለሆነ ነው የተቀጣሁት” በሚል አንዳችም ቅሬታ (ጥላቻ) አያሳድርም። በቦረና ክርስቲያኑና ሙስሊሙ በዚህ ባህላዊ ዳኝነት እሴት በመከባበር ተያይዟል::

### ሐ. ጂጌ/አዝማች

ጅጌ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ግለሰቦች ተሰባስበው የሚመሰርቱት ማህበራዊ ተቋም ነው። ተቋሙም በአንድ ግለሰብ ብቻ ሊሰሩ የማይቻሉ ጊዜና ጉልበት የሚወስዱ ከባድ ስራዎችን በጋራ ተባብሮ መስራት (የአንድ ግለሰብን ማሳ በጋራ ማረስ፣የደረሰ ሰብልን በጋራ ማጨድና መሰብሰብ፣የግለሰብን ወይም የአካባቢው መሪ የሆኑ ግለሰቦችን መኖሪያ ቤቶችና የእምነት መፈጸሚያ ቤቶችን በጋራ መስራት የመሳሰሉትን) የሚያስችል ማህበረ ፖለቲካዊተቋም ነው። ማህበረሰቡ እንደሚገልጸው ወንፈል ሁለትና ከሁለት በላይ በአብዛኛው የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች ተራ ገብተው የተለያዩ ስራዎችን የሚያከናውኑበት የስራ ባህል ነው። ይህም ዛሬ የአንዱን፣ነገየሌላውን፣ተነገወዲያ የዚያኛውን ስራ

ማከናወን ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ ወንፈል የስራ ብድር ማለት ነው።ብድር ስለሆነም አንዱ የሌላውን ብድር የመክፈል ግዴታ አለበት። ክፍያውየመጀመሪያው ግለሰብ እንደ ሁኔታው ካቀረበው ጉልበትና መስተ ንግዶ ሌላ ይዞት የመጣውንየስራ መሳሪያ ሁሉ ይጨምራል። በተቃራኒው ጅጌ ስራ የሰራልንን አካል እንድናግዘው ካልጠራን በስተቀር እንደወንፈል አይቆጠርም። በቦረና ቀደም ባሉት ዘመናት ሙስሊሙና ክርስቲያኑ በአንድነት በጂጌ መስጊድና ቤተክርስቲያን ለመስራት በጉልበትና በገንዘብ ሲደጋገፉ ኖረዋል። በበዓላቶቻቸው ላይም በእምነት ቦታዎች ላይ በመገኘት ደስታቸውን ሲገላለጹ ቆይተዋል (አቶ እስማኢል መኮንን፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 14/2016 ዓ.ም፤ አቶ ብርሀኑ ካሣሁን፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 23/2016 ዓ.ም)።

በቦረና ማህበረሰብ በትብብር መስራትን ከሚያበረታቱ ማህበረ ባህላዊ ተቋማት መካከል አንዱ “አዝማች” ነው። አዝማች በአካባቢው አንድ ሰው ልጁን ሲድር ሌላው ሰው በሰርጉ እለት ከ80-100 ሰዎችን የድግስ መስተንግዶ ወጪ (እንጀራ፣ ስጋ/ክክ ወጥ/፣ ጠላ/ቀሪቦ/ የዝግጅትና መስተንግዶ ጉልበት) በሙሉ ሸፍኖ ኃላፊነትን መወጣት ነው። በዚህም ባለድግሱ ልጁን ሲድር ብዙው የድግስ ወጪ አዝማች በሚይዙ ወዳጆቹና ጎረቤቶቹ ይሸፈንለታል። ከእሱ የሚጠበቀው ስንት አዝማች እንዳለው ቆጥሮ ለድግሱ የሚመጥን ሰው (ክርስቲያንም ሙስሊምም) በሰርጉ ላይ እንዲታደም መጥራትና ለባለ አዝማቾች የምስጋና ግብዣ ማዘጋጀት ብቻ ነው።

ይህ ባለጉዳይ ግለሰብ ታዲያ ይህን አዝማች የቱንም ያህል ጊዜ ቢቆይ ብድሩን የሚመልሰው አዝማች የያዘለት ጎረቤት ወይም ወዳጅ ልጁን ሲድር ነው። እርሱም በተራው አዝማች ይዞ ድግሱን በመደገስ ከ80-100 ሰው አብልቶ ብድሩን ይመልሳል። ሆኖም የአዝማች እዳ ያለበት ሰው ያ ጎረቤቱ ልጅ ሲድር በወቅቱ ካለው ሁኔታ አንጻር ችግር ላይ ቢሆን /ቢቸገር/ ከባለጉዳዩ ጋር በመመካከር አዝማቹን እንዲያወጣ አይገደድም። ባለጉዳዩ ሰው በርካታ አዝማች የሚኖረው ከሆነ በመመካከር አንድ አዝማች ሊያወጣ የሚችለው ገንዘብ ተሰልቶ ለባለጉዳዩ በጥሬ ገንዘብ በመስጠት እዳውን ሊከፍል ይችላል።

በቦረና ባህል መሰረት አዝማች ለማውጣት ክርስቲያን ወይም እስላም መሆን መስፈርት አይደለም። ዋናው ቁምነገር ስራውን ወይም ያጋጠመውን ጉዳይ በጋራ ለመስራትና ለመወጣት ዝግጁ ነው የሚለው ነው። በመሆኑም ይህ ጂጌ እሴት የቦረና ማህበረሰብን ሙስሊምና ክርስቲያን አማኞች ስራዎቻቸውን በጋራ በመስራትና በመተጋገዝ እንዲፈጽሙ አለፍ ሲል ደግሞ በመከባበርና በአብሮነት ለመኖር አስችሏቸዋል(አቶ ዩሱፍ እና አቶ አህመድቃለመጠይቅ የካቲት 12/2016፣አቶ እስማኢል፣ ቃለመጠይቅ የካቲት 14/2016)።

## 5. ማጠቃለያና ይሁንታ

### 5.1 ማጠቃለያ

ጥናቱ በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ እሴቶችን በመለየት ማስተዋወቅ ላይ ያተኮረ ነው። ጥናቱ በአብዛኛው ለአብሮነት መሰረት በሆኑ እሴቶችና የእሴቶቹ ባለቤት በሆነው ማህበረሰብ አኗኗር ላይ የተመሠረተ ነው። በመሆኑም ትኩረቱን በመቻቻል፤ በመከባበር፣ በመተባበር፣ በመተሳሰብ፣ በመተዛዘን፣ በመረዳዳትና በመደጋገፍ ላይ አድርጓል። አብሮ በመሥራት፣ አብሮ በመብላትና አብሮ በመጠጣት ላይ ያተኩራል።

በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በቦረና፣ በሙስሊምና ክርስቲያን ማህበረሰብ እንዴት እንደሚገለጽ ተጠንቷል። እንዲሁም ከማህበራዊ ኑሮ መስተጋብር አንጻር የሃይማኖት መቻቻል እሴት በቦረና ማህበረሰብ ምን ማለት እንደሆነና ምንን እንደሚያሳይ ተተንትኗል። ይህም የተደረገው የጥናቱን ጽንሰ-ሃሳብ፣ ንድፈ-ሃሳብና የጥናቱን ዘዴዎች መሰረት በማድረግ ነው።

ከጽንሰ-ሃሳብ አንፃር ፎክ ማለት በአንድ በሆነ የጋራ እሴት የተሳሰሩና የሚገናኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው:: "ሎር" የሚለው መርህ ደግሞ “የሰው ልጅ በማህበር ሲኖር የፈጠራቸውና የሚጠቀምባቸው የአሰራር፣ የአኗኗር፣ የአስተዳደር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ ወዘተ ዘዴዎች፣ ብልሃቶች፡፣ ፍልስፍናዎች፣ ጥበቦች፣ አመለካከቶች፣ እምነቶች፣ አምልኮዎች ወዘተ የሚለው አስተሳሰብ ተግባራዊ ተደርጓል።

ከዚህም ሌላ የእሴቶቹን ትርጉም፣ ምንነት፣ ፋይዳ፣ ተግባርና ጥቅም ተረድቶ፣ የማህበረሰቡን ስሜት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ማንነት፣ ፍልስፍና፣ አመለካከት ወዘተ ተገንዝቦ፣ በዚያው በአካባቢው፣ በባህሉና በማህበረሰቡ ኑሮ ላይ ተመስርቶ መረጃዎቹን ለመሰብሰብና ለመተንተን እንዲቻል፤ ጥናቱ በጠቀሜታዊነት የፎክሎር ንድፈሃሳብ መርህ ተመርቷል።

የጥናቱም ዘዴም አይነታዊ ነው። በዚህ ዘዴ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር እየተዛመዱ ገላጭ የምርምር ስልት ተተንትነዋል። የተተነተኑት መረጃዎችም ከባለቤቶቹ መንጭተው እዚያው የተቀዱና በባለቤቶቹ ድምጽ ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: በመሆኑም በተደረገው ምርምር የቦረና ማህበረሰብ ልዩ ልዩ

የሃይማኖት መቻቻል ስልቶችና ከስልቶቹ የሚመነጩ በርካታ የጋራ እሴቶች (ሀገረሰባዊ መድሀኒት፣ ሀገረሰባዊ እምነት፣ ሀገረሰባዊ ጋብቻ፣ እድር፣ ሀገረሰባዊ ዳኝነትና ጅጌ/አዝማች) እንዳሏቸው ለማረጋገጥ ተችሏል።

በጥናቱ ውጤት መሰረትም የመቻቻል እሴቶቹ በተለይም በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል “መቻቻል” የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ፣መርህና ተግባራዊ ድርጊቶችየሚያካትቱገጽታዎችን( አንዱ የሌላውን ህልውና ተቀብሎ እውቅና መስጠትን፣መተሳሰብን፣መረዳዳትን፣መተባበርን፣አብሮነትን፣አንድነትንና ሰላምን ወዘተ) ለማምጣት አወንታዊ ጠቀሜታ እንዳላቸው ተመላክቷል።

## 5.2 ይሁንታ

በወሎ ቦረና በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰቦች መካከል ለረዥም ጊዜ አብሮ በመኖር ሂደት የተፈጠሩና ተቀባይነት ያገኙ ፎክሎራዊ የመቻቻል እሴቶች አሉ።በጥናቱ በደቡብ ወሎ ቦረና ወረዳ የመቻቻል እሴቶች በርካታ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ ሀገረሰባዊ መድሀኒት፣ ሀገረሰባዊ እምነት፣ ሀገረሰባዊ ጋብቻ፣ እድር፣ ሀገረሰባዊ ዳኝነትና ጅጌ/አዝማች ተተንትነዋል። ይህ የሆነበት ምክንያትም እሴቶቹ ለሃይማኖት መቻቻል አስተዋጽዎ አላቸው ተብሎ በመታመኑ ነው።

በጥናቱ ውጤት መሰረትም የመቻቻል እሴቶቹ በተለይም በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል “መቻቻል” የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ፣መርህና ተግባራዊ ድርጊቶች በአጠቃላይእውነተኛ ትርጉም የሚያካትቱ ገጽታዎችን(አንዱ የሌላውን ህልውና ተቀብሎ እውቅና መስጠትን፣መተሳሰብን፣መረዳዳትን፣ መተባበርን፣ አብሮነትን፣ አንድነትንናሰላምን ወዘተ) የሚያጠናክሩ መሆናቸው ተገልጿል።

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች በአጥኚው ተሰንዝረዋል።

1. በመማሪያመጻህፍት አዘጋጆች መቻቻልን የሚያሳዩ ባህላዊ እሴቶችን በምንባብ፣ ቲያትር አዘጋጆችም በጭብጥነት በማካተት ባህሉን ለታዳጊ ልጆች ማስተዋወቅ ቢቻል፣
2. የመቻቻል እሴቶች በተለያዩ ምክንያቶች እየተሸረሸሩና እየተዳከሙ በመሄድ ላይ እንደሆኑ የእሴቶቹ ባለቤቶች ይናገራሉ። በመሆኑም ምክንያቶቹን ከስረ-መሰረታቸው አውቆ መፍትሄ ለማበጀት በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ጥናትና ምርምር ቢካሄድ፣
3. በቦረና የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች ከጊዜ ወደጊዜ እየተረሱ ነው። ከዚህ አንፃር ከቤተሰብ ጀምሮ የሀይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ አካላት ትውልዱ እሴቶቹን እንዲያውቃቸው፣ እንዲጠብቃቸውና እንዲጠቀምባቸው በኃላፊነት ቢያስተምሩ፣

4. በአካባቢውና በየደረጃው የሚገኙ ሃይማኖት ጉባኤዎች በየአጋጣሚዎቻቸው በመከባበር ላይ ውይይት በማድረግ ለተከታዮቻቸው በተከታታይ ግንዛቤ ቢፈጥሩ የመከባበር እሴቱን ማስቀጠል ያስችላል።

## ዋቢ ጽሁፎች


ሠሎሞን ተሾመ። (2007)። **ፎክሎር፤ ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ።**አዲስአበባ፣ በሌ ማተሚያ ድርጅት።

የኢትዮጵያ ኃይማኖቶች ጉባኤ። (2014)። መቻቻል፣ ሠላምና መከባበር ማሰልጠኛ ማንዋል። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ደስታ ተክለወልድ።(1962)።**አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት።**አዲስአበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ጌታዋ ሞላ። (2008)። የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ምንጩ፣ መገለጫዎቹና ተግባሩ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/።

ፈቃደ አዘዘ። (1991)። **የስነ-ቃልመምሪያ።**አዲስአበባ፣ በሌ ማተሚያ ድርጅት።

ፍሬህይወት ባዩ። (2018)። **Zena-Lissan** Vol XXVII No 1. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ።

የበረና ወረዳ አስተዳደር ።(2015)። አጠቃላይ መረጃ። (ያልታተመ)።

Abbink, Jhon. (1998). An Historical-anthropological Approach to Islam in Ethiopia: Issues of Identity and Politics**; Journal of African cultural studies**, Volume11, Leiden.

Abdullah, T. (2012). “Co-existence and Harmony in a Pluralistic world: Gulen Movement as Wording model,” a paper presented at a conference one stablishing and sustaining the culture of co-existence and mutualunderstanding organized by Ministry of Ethiopian Federal Affairs. /Unpublished/.

Braukamper, Ulrich. (1992). Religious Syncretism in Southern Ethiopia, **Journal of religion in Africa,** Vol.22, No.3.

Lian, H., Ferris, D.L. and Brown, D.J., (2012). Does power distance exacerbate or mitigate the effects of abusive supervision?.**Journal of applied psychology**, vol. *97*, No. 1.

Murphy, A. (1997). “Toleration, and Liberal Tradition,” **Journal of Polity**, vol. 29, No. 4.

Newman, J. (1978). “Idea of Religious Tolerance”. **Journal of American Philosophy**,Vol. 15, No.3.

UNESCO. (1995). **Declaration of Principles on Tolerance;**Proclaimed and Signed by the Member States of UNESCO, Paris.